## ምዕራፍ አንድ

## ቋንቋና ህብረተሰብ

### ቋንቋ ምንድን ነው?

ስለ ቋንቋ ምንነት አብዛኛው ሰው የሚሰጠው ምላሽ ‹‹ቋንቋ የመግባቢያ ነው ››የሚለው ነው ይህ አባባል በብዙ ሰዎች ዘንድ የተለመደ ሁለት መሰረታዊ የሆኑ የግንዛቤ ስህተቶችን ሊያስከትል ይችላል፡፡

አንደኛው መግባባት በቁሳዊና በአካላዊ እንቅስቃሴዎችም ሊከናወን ስለሚችል እነዚህም ቋንቋ ናቸው ወደ ሚለው አስተሳሰብ ያመራል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ መግባባት ማስቻል የቋንቋ ተግባር ቢሆንም መግባቢያ የሚለው አነጋገር የቋንቋን ተግባር እንጂ የቋንቋን ምንነት አያመለክትም፡፡ይህ ማለት ቋንቋ መግባቢያ ነው የሚለው ምላሽ አገልግሎቱን እንጂ ውስጣዊ ባህሪውን የሚያመለክት አይደለም ፡፡

በመሆኑም የቋንቋ ምንነት በሳይንሳዊ መንገድ ስንመለከተው፡-ቋንቋ ከሰዎች አንደበት የሚፈልቅ ስረዓት ባለው መንገድ እየተቀናጀ አንዳች መልዕክት የሚያስተላልፈውን ማለታችን ነው፡፡

በሳይንሳዊ ምርምር ያንድንነገር ምንነት ማሳየት ሲፈለግ ደግሞ ጉዳዩን ከሚመሰርቱ ንጥረ ነገሮች ባህረይ ትንታኔ መነሳት የተለመደ ነው፡፡ከዚህ አኳያ ሲታይ የቋንቋ ሊቃውንት ሁሉ ስለ ቋንቋ ምንነት ሲያወሱ ቋንቋ ንግግር መሆኑንና የንግግር መሰረቱ ወይም ንጥረ ነገሩ ደግሞ ድምፅ መሆኑን ያምናሉ፡፡ የቋንቋ ወይም የንግግር መሰረቱ ድምፅ ነው ሲባልም በማንኛውም ቁሳዊ አካል እንቅስቃሴ የሚፈጠረውን መካኒካዊ ድምፅ ሳይሆን በሰው ልጅ አንደበት የተነገረና ስረዓት ባለው መንገድ እየተቀናጀ አንዳች መልዕክት የሚያስተላልፈውን ማለታችን፡፡

### የቋንቋ አገልግሎት

ቋንቋ እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ ሁለት ተግባራት አሉት፡፡አንደኛው ሐሳብን ማስተላለፍ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከሚነገረው ሐሳብ ጋር ተያይዞ የሚተላለፈው የተናጋሪው ማንነት ነው፡፡በመሆኑም ቋንቋ ስነ ልሳናዊና ማህበራዊ አገልግሎት አለው፡፡

- የቋንቋ ስነ ልሳናዊ አገልግሎት፡- ማግባባት ሲሆን
- የቋንቋ ማህበራዊ አገልግሎት፡- የተናጋሪውን ማንነት መግለፅ ነው፡፡

ባጭሩ የቋንቋ ተግባር ልምድን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ ነው፡፡

## መደበኛና ኢመደበኛ ቋንቋ

ቋንቋ በአጠቃቀም ጊዜ ሁለት መልኮች አሉት፡፡እነሱም መደበኛና ኢመደበኛ ናቸው፡፡

**መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም፡-** በሰዋስዋዊ ቅንብሩ ፣ በቃላት አመራረጡ ፣ በአጀማመሩና በአጨራረሱ ይሄዳል፡፡ ተቀባይነት ባለው ልማዳዊ አቀራረብ ይታገዛል፡፡ለተለያየ ቦታና ጊዜ ተስማሚና አመቺ

አቀራረብ ይዞ በንግግር ይደመጣል፤በፅሁፍ ይነበባል፡፡

መደበኛ ቋንቋ ከሚንፀባረቅባቸው መካከል የሰርግ ጥሪ ወረቀት፣ማመልከቻ፣የፍርድ ቤት ሐተታሴወዘተ ይጠቀሳሉ፡፡

**ኢመደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም፡-** ለሀሳብ ቅደም ተከተሉ፣ለድምፀቱ መለዋወጥ፣ለሰዋስዋዊ ቅንብሩ ፣ለቃላት መረጣው፣ሴእምብዛም ጥንቃቄ አያደርግም፡፡ የተለመደውን አባባል ካልተለመደው ጋር ያደባልቃል፡፡

ለምሳሌ፡- የፍቅረኛሞች ንግግር ቅርበት ያላቸው ሰዎች ንግግር

### ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ ምላሽ ስጡ፡፡**

1. ቋንቋ ምንድን ነው
2. የቋንቋ አገልግሎት ምንድን ነው
3. የቋንቋን መደበኛና ኢመደበኛ አጠቃቀም አስረዳ/ጂ/

## ምዕራፍ ሁለት

## 2. ስነ ቃል

ስነ ቃል የስነ ፅሁፍ አንዱ ዘርፍ ነው፡፡ ስነ ቃል በመነገር በመተረት ወይም በመዜም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች የሚቀርብ ነው፡፡ ስነ ቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ሲነገር የኖረ የቃል ስነ ፅሁፍ ነው፡፡ በመሆኑም በቃል የሚከወኑ የቋንቋ ጥበቦችን የሚያጠና የስነ ፅሁፍ ዘርፍ ነው፡፡ ስነ ቃል የአንድን ማህበረሰብ ወግ፣ እምነት፣ ባህል፣ አመለካከት፣ ፍልስፍና፣

የአኗኗር ዘይቤ፣ ወዘተ.ያንፀባርቃል፡፡ ማህበረሰቡ ሀዘን ደስታውን፣ ረሀብ ጥማቱን፣ ማግኘት ማጣቱን፣ ምኞት ተስፋውን፣ ወዘተ. በስነቃል ይገለፃል፡፡

በስነ ቃል ስር የሚመደቡትን ጥቂት ምሳሌዎች ስንመለከት ተረቶችን፣ እንቆቅልሾችን፣ ቃላዊ ግጥሞችን፣ አፈ ታሪኮችን ፣ ምሳሌያዊ ንግግሮችን፣ ሀተታ ተፈጥሮዎችን ና ዝማሬዎችን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡

**ተረት** ፡-ሶስት ክፍሎች አሉት መግቢያ አካልና መደምደሚያ ሊባሉ ይችላሉ፡፡ በመግቢያ ክፍል ውስጥ አድማጭ ይነቃቃበታል በዚህ በመግቢያ ክፍል ውስጥ ገፀባህርያት መቼትን ያስተዋውቃል፡፡መቼትን በሚመለከት ላቅ ያለ ዘመንን ከመጥቀስ ባሻገር ውስን ቦታና ጊዜን አይጠቅስም፡፡

በተረት ውስጥ የምናገኛቸው ገፀ ባህርያት እንሰሳት ወይም አራዊት ሰዎች ፣ከገሃዱ አለም ወጣ ያሉሰዎችንም እናገኛለን፡፡በተረት ውስጥ እንሰሳት ወይም አራዊት የሰውን ባህርይ ተላብሰው ሲንቀሳቀሱ እናገኛለን በሌላ አገላለፅ እነደ ሰው ሲናገሩ፣ሲያዝኑ ፣ ሲደሰቱ፣ ሲያፈቅሩሔ.ወዘተ እናገኛለን፡፡ በተረት ውስጥ የምናገኛቸው ሰዎች በጣም የተጋነኑ ናቸው፡፡ብልጥ ከሆኑ የመጨረሻ ብልጦች ወይም ሞኞች ፣ጀግኖች ወዘተ ሆነው እናገኛቸዋለን ተረት ውስጥ ታምራት ይበዛበታል፡፡

**አፈ ታሪክ፡-** አንዱ በዝርው የሚቀርብ የስነ ቃል ዓይነት ነው፡፡እውነት የሆነን ነገርን መሰረት ያደርጋል፡፡በታሪክ ውስጥ በአንድ ወቅት በትክክል በተደረገ ነገር ላይ ይመሰረታል፡፡አፈ ታሪክ የሚነገርበት ዋናው ምክንያት ለማስተማር ነው ይባላል፡፡አፈ ታሪክ የራሱ የሆነ ማህበራዊ አጋጣሚ የለውም የሚነገረው በጨዋታ በንግግር ውስጥ ነው፡፡

**ሀተታ ተፈጥሮ፡-** ለተፈጥሮ ክስተቶች መልስ የምንሰጥበት የስነ ቃል ዓይነት ነው፡፡አንድን ነገር ከምን የመጣ ነው ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ የስነ ቃል ዘርፍ ነው፡፡

**እንቆቅልሽ፡-** የአንድን ነገር ባህርይ የሚገልፅ ምንነቱን ማንነቱን የሚያስር ነው ለማለት ይቻላል፡፡እንቆቅልሽ ከተረት ፣ ከአፈ ታሪክና ከሀተታ ተፈጥሮ አንፃር ሲታይ በአጫጭር የሚቀርብ ነው፡፡እንቆቅልሽ የራሱ የሆነ የአጨዋወት ስርዓት አለው፡፡ለተዝናኖትም ለማስተማርም የሚነገር ነው፡፡እንቆቅልሽ እራሱን ችሎ የሚነገር ነው፡፡እንቆቅልሽ የልጆች ቸዋታ ነው፡፡በጥያቄና መልስ የሚካሄድ ሲሆን የልጆችን የመመራመር ችሎታ ለማዳበር የሚከወን ነው፡፡የሚከወንበት የራሱ የሆነ አጋጣሚ አለው በትርፍ ጊዜ ነው፡፡

- እንቆቅልሽ የልጆችን የመራመር ችሎታ ለማዳበር ያግዛል
- የተሳታፊን አእምሮ የሚያሰላ ነው

አከዋወኑም ፡- ጠያቂ ፤እንቆቅልህ/ሽ/ብሎ ሲጠይቅ

መላሽ፤ምን አውቅልህ/ሽ/በማለት እንዲጠይቅ ይጋብዛል

**ምሳሌያዊ አነጋገር፡-** ግጥማዊ ድምፀት ባላቸው በአጫጭር ሐረጎችና ዐ.ነገሮች የሚዋቀሩ ሲሆን ለአንድ ማህበረሰብ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ላቅ ያለ ነው፡፡

- ማህበረሰቡ የማይፈቅዳቸውን ባህርያት ለመኮነን
- ትጉሓንን ለማበረታታት
- ጀግንነትን ለማደፋፈር
- በጎ ስነ ምግባርን ለማስተማር ሔ. ከፍተኛ ግልጋሎት ይሰጣሉ፡፡

ለምሳሌ ፡ሲሮጡ የታመቁት ሲሮጡ ይፈታል፡፡ የችኮላን መጥፎነት ያስተምራል

## 2.1 . የስነ ቃል ባህርያት

ስነ ቃል ከተፃፈው ስነ ፅሁፍ የሚለይበት የራሱ ባህርያት አሉት ከነዚህ መካከል ክዋኔ ፣ አወዳዊነት፣ ተለዋዋጭነትና ህዝባዊነት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡እነዚህን አራቱን የስነ ቃል ባህርያት ለምሳሌ ተረትን በመውሰድ እንመልከት፡-

ተረት በአንድ በተወሰነ ቦታና ጊዜ የሚከወን ነው፡፡ስለዚህ ከዋኙና ተደራሲያን  በአንድ ቦታ ተገናኝተው የሚያደርጉት የተረት ክወና ከዋኙ ቋቋረት ተረትቋቋሲል ተደራሲያን ቋቋላም በረትቋቋ ወይም ቋቋመሰረትቋቋ በማለት ይመልሳሉ፤ይሳተፋሉ፡፡በመሆኑም ይህ ክዋኔን ያመለክታል፡፡በክዋኔ ጊዜ ተደራሲያን ቋቋሺ›› ‹‹ከዚያስቋቋ ወዘተ እያሉ ይሳተፋሉ፡፡በዚህ ዓይነት ተደራሲያን የአጃቢነት፣ የመላሽነትና የአድማጭነት ተግባርን ይወጣሉ፡፡ስነ ቃል ካልተከወነ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊተላለፍ አይችልም፡፡ስነ ቃል ራሱ የሚፈጥረው በሚከወንበት ጊዜ ነው፡፡ በተወሰነ ማህበራዊ አጋጣሚ ላይ ከደራሲ ለተደራሲ በድርጊት በሚቀርብበት ጊዜ ነው፡፡

በኣንፃሩ ከዋኙ ተረቱን ከወላጆቹ ወይም ከሌሎች ሰዎች የሰማው ሊሆን ይችላል፡፡ነገር ግን ልክ እሱ መጀመሪያ እንደሰማው ሳይጨምርና ሳይቀንስ እንዳለ አይተርክም፡፡ከዚህ ይልቅ በራሱ አባባልና አንዳንዴም በዘነጋቸው የተረቱ ክፍሎች ምትክ የራሱን እየፈጠረና እየሞላ ይናገራል፡፡ይህ ሁኔታ የስነ ቃልን **ተለዋዋጭነት** ያመለክታል፡፡

ለስነ ቃል መለዋወጥ አንዱ ምክንያት የሰው ልጅ የማስታወስ ችሎታ ውስን መሆን ነው ማለት ይቻላል፡፡አንዱ አቀንቃኝ በአንድ በተወሰነ ማህበራዊ አጋጣሚ ላይ የተጠቀመባቸውን ቃላትና ድርጊቶች በሙሉ ሌላው አቀንቃኝ ላያስታውስ ይችላል፡፡በዚህም የተነሳ በማያስታውሳቸው ቃላትና ድርጊቶች ምትክ አዳዲስ ምትክ አዳዲስ ቃላትና ድርጊቶችን ያስገባል፡፡ለስነ ቃል

መለወጥ ሌላው ምክንያት ከሚነገርበት አውድ ጋር ለማስማማት ነው፡፡የስነቃልን ተለዋዋጭነት አንድ ምሳሌ ወስደን እንይ

1. ትመጫለሽ ብዬ ሳይ ማዶ ሳይ ማዶ፣

   የልጅነት ዓይኔ ሟሟ እንደ በረዶ፡፡

2. ትመጫለሽ ብዬ ሳይ ማዶ ሳይ ማዶ፣

   ዓይኔ ተበላሸ ቀልጦ እንደ በረዶ፡፡

ለውጡ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ሊሆን ይችላል፡፡ለውጡ በቃል ፣በሀረግ፣በአረፍተ ነገር ወይም በአገላለፅ ደረጃ ሊሆን ይችላል፡፡

ሌላው የስነ ቃል አወዳዊነት ነው ተረቱ ማታ ማታ ወላጆች ለልጆቻቸው ይተርቱት ይሆናል፤ወይም በክፍል ውስጥ አንድ ተማሪ ለጓደኞቹ የሚተርተው ሊሆን ይችላል፡፡ተረቱ የሚነገርበት ቦታና ሁኔታ የስነ ቃልን አወዳዊነት ያሳያል፡፡ እያንዳንዱ ስነ ቃል የሚቀርብበት ወይም የሚከወንበት የራሱ የሆነ ማህበራዊ አጋጣሚ አለው፡፡

ህዝባዊነት ስነ ቃል የህዝብ ወይም የማህበረሰቡ ነው የእኔ ነው ባይ ደራሲ የለውም ወይም አይታወቅም ማንም የማህበረሰቡ አባል በስነ ቃል ሊጠቀም ይችላል፡፡

## 2.2. የስነ ቃል ተግባር

ስነ ቃል ፈጥሮ ለሚገለገልበት ማህበረሰብ የተለያዩ ተግባራትን ይወጣል፡፡የስነ ቃልን ተግባራት በአምስት አባይት ክፍሎች ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡እነሱም፡-

1. የመግለጥ ተግባር
2. የማጠናከር ተግባር
3. የመትከል ተግባር
4. የማስተማር ተግባር
5. የመግታት የመቆጣጠር ተግባር ናቸው፡፡

### 2.2.1 የመግለጥ ተግባር

ገላጭ ትረካዎች በያካባቢው ለሚኖሩ ሰዎች መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የሚሞክሩ ናቸው፡፡ አካባቢያቸውን፣ ሰውን፣እንሰሳትን፣እፀዋትን ማን ፈጠራቸው እያሉ ለሚጠይቋቸው ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ይሞክራል፡፡

**ለምሳሌ፡-** ሀተታ ተፈጥሮ ፣ ተረትሔ..

### 2.2.2 . የማጠናከር ፣ የመትከል ተግባር

ማህበራዊ ድርጅቶቻቸውን እና ልዩ ልዩ ባህሎቻቸውን በስነ ቃል አማካይነት ያጠናክራሉ፡፡ ከልደት እስከ ሞት የሚያከናውኗቸውን ድርጊቶች አስፈላጊነትና ተገቢነት እያሳመኑ ክንዋኔዎቹ እንዳይጠፉ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ፡፡

**ለምሳሌ፡-** ያሉት ከሚጠፉ የወለዱት ይጥፉ

### 2.2.3. የማምለጥ ተግባር

የሰው ልጅ ከወትሮው የዕለት ተዕለት የህይወት ውጣ ውረድ ማምለጥ ይፈልጋል ከአሰልቺና ከተደጋጋሚ የህይወት ክስተቶች ሸሽቶ በምናቡ አዲስ ዓለም ውስጥ መግባት ይሻል፡፡

### 2.2.4. የማስተማር ተግባር

ስነ ቃሎች ስለ ልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዮችና ስለ አኗኗር ስርዓት ያስተምራሉ፡፡ የአበላል ፣ የአጠጣት ፣ የአለባበስ፣ የአቀማመጥ ፣ የአነጋገር ፣ የአካሄድ ስርዓትን ፣የትጋትን ቈለጋስነትን ፣የህብረትን ጥቅም ሔ.ወዘተ ይሰብካሉ፡፡

**ለምሳሌ፡-** ድር ቢያብር አንበሳ ያስር የመተባበርን ጥሩነት ያስተምራል፡፡

### 2.2.5 . የመግታት - የመቆጣጠር ተግባር

የአኗኗር ብልሃትንና በጎ ምግባርን ያስተምራሉ ያልናቸው ስነ ቃሎች የመጥፎ ባህርያትን መስፋፋትም ሲቆጣጠሩ ይገኛሉ፡፡በመሆኑም ስነ ቃሎች ስርቆትን፣ መዋሸትን ፣ ስስትን፣ ክፋትን፣ ፈሪነትን ይገስፃሉ፡፡በቀልድ ዘፈኖችና ትረካዎች አማካይነት በእነዚህ ጠባያት ይሳለቁባቸዋል ፣ ያጥላሏቸዋል ፣ ያላግጡባቸዋል፡፡

**ለምሳሌ፡-** ከስስታም አንድ ያንቀው ፣ አንድ ይወድቀው፡፡

አታላይ ለጊዜ ያመልጣል በኋላ ይሰምጣል፡፡

ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል

### የስነ ቃል ዘውጎች

ስነ ቃል ቅርፅን ዋነኛ መሰፈርት በማድረግ በሶስት ዘውጎች ይከፈላል፡፡ እነሱም ዝርውቃል ትረካ፣ቃል ግጥምና አጫጭር ቅርፆች የሚባሉት ናቸው፡፡

**በዝርው ቃል ትረካ ስር** ፡- ተረት ፣ ሀተታ ተፈትሮዎች፣አፈ ታሪኮች ይጠቀሳሉ፡፡

**ቃል ግጥም**፡-ቀረርቶ፣ሙሾ፣ሆታ፣ልመናዬ..ኛቸው።

**አጫጭር ቅርፆች** ፡-ምሳሌያዊ አነጋገር፣እንቆቅልሽ፣ቀልዶችዬዬ ይጠቀሳሉ።

## ምዕላድ

ምዕላድ አነስተኛው የቃል ደረጃ ሲሆን በቂ ትርጉም ተሸክሞ የሚያግባባ ነው።

- ምዕላድ ትርጉም ወዳለው ሌላ ቃል አይከፈልም ወይም አይሸነሸንም።
- ምዕላድ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሊከፈል ይችላል።እነሱም ነፃ ምዕላድና ጥገኛ ምዕላድ ናቸው።

  - **ነፃ ምዕላድ**፡-ራሳቸውን ችለው የቋንቋውን ተናጋሪ በሚገባ ሊያግባቡ የሚችሉ ቃላት ናቸው።ለምሳሌ ጦር ፣ በግ ፣ዶሮ፣ ወዘተ በነፃ ምዕላድ ስር የሚመደቡ ናቸው። ነፃ ምዕላዶች ስርወ ቃል ፣ ግንድ ፣ዋና ቃል ፣ ዐምድ በመሳሰሉ የተለያዩ ስያሜዎችም ይጠራል።
  - **ጥገኛ ምዕላድ** ፡-በራሳቸው ትርጉም ባይኖራቸውም በዋናው ቃል ላይ እየታከሉ ትርጉም ይሰጣሉ።ለምሳሌ ፤ጦር-ኤ  ጦሬ፣ ልብስ - ኤ  ልብሴ ወዘተ በማለት /-ኤ/የመሳሰሉ አናባቢዎች በማከል የእኔ የሚል ትርጉም እንዲሰጡ ማስፋፋት ይችላል።  ጥገኛ ምዕላዶች በሁለት ይከፈላሉ።እነሱም የእርባታ ምዕላድና መስራች ምዕላድ ናቸው።

    - ✓ **የእርባታ ምዕላድ** ፡-በቃሉ ላይ ሲታከሉ ቃሉን ወደ ሌላ የቃል ክፍል አይቀይሩም።

      ለምሳሌ፡በግ - በጎች   /-ኦች/

      ቤት - ቤቴ  /-ኤ/ ከምሳሌው እንደተረዳነው በግ ና ቤት የቃል ክፍላቸው ስም ነው።እንዲሁም በጎች ና በቴ የቃል ክፍላቸው ስም ነው።ስለዚህ /-ኦች/ ና /-ኤ/ የእርባታ ምዕላዶች ይባላሉ።

    - ✓ **መስራች ምዕላድ** ፡-በቃሉ ላይ ሲታከሉ የቃሉን ክፍል ወደ ሌላ የቃል ክፍል ይቀይራሉ።

      ለምሳሌ፡ልብ  - ልባም         /-አም/

      ሰማይ - ሰማያዊ     /-አዊ/ ከምሳሌው እንደምንረዳው ልብ ና ሰማይ የቃል ክፍላቸው ስም ሲሆን ቅጥያ የወሰዱት ልባም ና

ሰማያዊ የቃል ክፍላቸው ቅፅል ነው፡፡ በመሆኑም /-አም/ ና /-አዊ/ መስራች ምዕላድ ናቸው፡፡

**የጥገኛ ምዕላድ ተግባር**

ጥገኛ ምዕላዶች በቃል ላይ ሲታከሉ የተለያየ ተግባር አላቸው፡፡ ከተግባሮቹም ውስጥ የሚከተሉትን እንመልከት

❖ **ቁጥርን አመልካች** ፡- በአማርኛ ቋንቋ ብዛት ለማመልከት የሚገቡ ጥገኛ ምዕላዶች ሁለት ናቸው፡፡እነሱም /-ኦች/ ና /ዎች/ ናቸው፡፡

- **-ኦች** ፡-በሳድስ ድምፅ በማያልቁ ቃላት ላይ በመግባት ብዛትን ያመለክታል፡፡

ለምሳሌ፡- ላም ላሞች / -ኦች/

ከብት ከብቶች / -ኦች/

በግ በጎች /-ኦች/

ም፣ት፣ር፣ግ ሳድስ መሆናቸውን ልብ በሉ፡፡

- **-ዎች** ፡- ከሳድስ ውጭ ባሉ ድምፆች በሚያልቁ ቃላት ላይ በመግባት ብዛትን ያመለክታሉ፡፡

ለምሳሌ፡- መኪና መኪናዎች / - ዎች/

ተማሪ ተማሪዎች /- ዎች/

ተላላኪ ተላላኪዎች /- ዎች/

**ልብ በሉ** ተማሪ፣መኪና፣ተላላኪ፣ወዘተ የመሳሰሉ ቃላት /-ኦች/ የአብዢ ቅጥያ የማይወስዱት በአማርኛ ቋንቋ ህግ ሁለት አናባቢዎች ተከታትለው ስለማይመጡ ነው፡፡

❖ ወገንን አመልካች ፡- ለምሳሌ፡ ኬንያዊ /-አዊ/

ዘመናዊ /-አዊ/

❖ ፆታን ማመልከት ፡- ለምሳሌ፡ ልጂት /-ኢት/

ሙሽሪት /-ኢት/

❖ ዓይነትንና ባህርይን ማመልከት ፡ ለምሳሌ፡ እሾሃማ

/-አማ/   ዓይነትን ማመልከት

ሆዳም      /-አም/  በህርይን ማመልከት

- ❖ ባለንብረትነትን ማመልከት ፡-        ለምሳሌ፡   ኮቴ       /-ኤ/

ኮትህ     /-ህ/

- ❖ ታዋቂነትን ማመልከት ፡-       ለምሳሌ፡   ቤቱ      /-ኡ/

ጨረቃዋ     /-ዋ/

**ምዕራፍ ሶስት**

**ስነ ፅሁፍ**

ስነ ፅሁፍ የሰውን የተለያዩ ገጠመኞችና የኑሮ መልኮችን ሊያሳይ የሚችል የሰዎች ሀሳብ መገለጫ ነው፡፡ሰዎች ስለራሳቸው ስለህይወት የሚሰማቸውን ፤ የሚያስቡትንና የሚመኙትን በአጠቃላይ ግንዛቤያቸውን በቋንቋ አማካይነት የሚያንፀባርቁበት ኪነ ጥበብ ነው፡፡

- ➢ የኪነ ጥበብ ስራ በመሆኑ ውበት አለው
- ➢ ስሜትን ይነካል ፤ ይማርካል ፤ያስደስታል፡፡
- ➢ በስነ ፅሁፍ የሚገለፀው የሰው ልጅ ህይወት ነው፡፡

ስነ ፅሁፍ በተለያዩ ቅርፆች በቋንቋ አማካይነት የሚከሰት፤ስለሰዎች በሰዎች ለሰዎች የሚዘጋጅ የገጠመኝ ማንፀባረቂያና ህይወትንና እውነትን በአንድ አጣምሮ የሚይዝ ህልውናው በቃልም በፅሁፍም የሆነ የፈጠራ ስራ ነው፡፡

- ❖ በስነ ፅሁፍ ውስጥ ሊመደቡ የሚችሉት
  - ➢ ልቦለድ
  - ➢ ስነ ግጥም
  - ➢ ተውኔትና
  - ➢ ስነ ቃል ናቸው፡፡

**የውይይት  ምንነት ፣ አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያ**

የውይይት ምንነት ፡- ውይይት በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተለያየ አመለካከት ያላቸው ሰዎች

ሀሳባቸውን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመግለፅ የሚጠቀሙበት ንግግር ነው። ሰዎች ችግር ሲያጋጥማቸው በመወያየት ለችግሮች መፍትሄ ይፈልጋሉ።

**የውይይት አዘገጃጀት መመሪያ**

- ለውይይት የሚቀርበውን ርዕስ በሚገባ ማጤን፣
- በርዕሱ ዙሪያ ዕውቀት ያላቸው ሰዎችን መጠየቅ፣ ማማከር ፣ የተለያዩ መፃህፍትን ማንበብ፣
- ከተለያዩ የመረጃ ምንጭች የተገኙ ፍሬ ሀሳቦችን በቅደም ተከተል ማደራጀት፣
- በውይይት ጊዜ የሚደረገው የቋንቋ አጠቃቀም ፣ የቃላት ምርጫ ለአድማጩ የሚመጥን እንዲሆን መዘጋጀት፣
- ዝግጅቱ ወቅታዊና ጠቃሚ መሆኑን ማረጋገጥ፣

**የውይይት አቀራረብ መመሪያ**

- አለባበስን አስተካክሎና ንፅህናን ጠብቆ በውይይቱ ቦታ መገኘት፣
- ተራ ጠብቆ መናገር፣
- የሌሎችን ሀሳብ ማክበር፣
- ያልተንዛዛና ምጥን አስተያየት መሰንዘር፣
- ሲናገሩ ድምፅን መመጠን፣
- ፍርሃትና ግዴለሽነትን ማስወገድ፣
- የውይይቱን ጭብጦች በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፣
- እኔ ብቻ ላውራ የሚል አስተሳሰብን ማስወገድ፣

**አንቀፅ**

በአንድ መሰረታዊ ሀሳብ ላይ የሚያጠነጥኑ ፣ እርስ በርስ ተያያዥነት ያላቸው ዐ.ነገሮች የሚገኙበት አካል ነው። አንድ ነጠላ ሀሳብን ለመግለፅ ሲባል ፣ በቁጥር አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሀሳብ ተዛምዷቸውን የጠበቁ ዐ.ነገሮች የሰፈሩበት የድርሰት ቅርፅ ነው።አንቀፅ ብዙውን

ጊዜ አንድ ኀይለ ቃል እና ከአንድ በላይ መዘርዝር ዐ.ነገሮችን ሊይዝ ይችላል፡፡

ፅሁፍ በአንቀፅ የሚከፋፈልበት ዋና ዋና ምክንያቶች፡-

- እያንዳንዱ አንቀፅ በውስጡ የሚይዙት ሀሳብ የተለያየ በመሆኑ
- አሰልቺነትን ለማስወገድ ሲባል ፅሁፍ በአንቀፅ ይከፋፈላል፡፡
- በአንቀፅ የተከፋፈለ ፅሁፍ ውበት ይኖረዋል፡፡ዓይን መልካም ነገርን ማየት ይፈልጋል፡፡

**የአንቀፅ ባህርያት**

አንድ ጥሩ አንቀፅ የሚከተሉትን መሰረታዊ ባህርያት ይዞ መገኘት አለበት፡፡ እነሱም፡-

- አንድነት ወይም ወጥነት
- ግጥምጥምነት
- ብርታት ወይም ብቃት
- ኀይለ ቃል ናቸው፡፡

**አንድነት ወይም ወጥነት**፡- ሲባል በአንድ አንቀፅ ውስጥ የሚገኙት ዐ.ነገሮች የሚያነሱት ሀሳብ በአንድ መሰረታዊ ጉዳይ ላይ ብቻ የሚያተኩር መሆን አለበት ማለታችን ነው፡፡

**ግጥምጥምነት** ፡- በአንቀፅ ውስጥ ያሉ የሀሳብ ሰንሰለታዊ ቁርኝት ማለት ነው፡፡

**ብርታት ወይም ብቃት** ፡- ስንል አንድነትንና ግጥምጥምነትን ጠብቆ የቀረበው ሃሳብ ጥልቀቱ ምን ያህል ነው፡፡ የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም የቃላት ምርጫ ፣ የዐ.ነገር አወቃቀር ፣ የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም ፣ የገለፃ ብቃት የመሳሰሉት ግምት ውስጥ የሚገቡ ናቸው፡፡

**ኃይለ ቃል** ፡- የአንቀፁን ሃሳብ አጠቃሎ የያዘ ዐ.ነገር ነው ፡፡ በአንቀፅ ውስጥ ኃይለ ቃሉ የሚገኝበትን ቦታ መሰረት በማድረግ አራት የአንቀፅ ቅርፆች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡









## ስርዓተ ነጥቦች

እንደ ማንኛውም ቋንቋ የአማርኛ ቋንቋም ለፅህፈት የሚያገለግሉ የራሱ ስርዓተ ነጥቦች አሉት፡፡ እነዚህ ስርዓተ ነጥቦች በወረቀት ላይ የሰፈረ ሀሳብ (ቋንቋ) መልዕክቱ ግልፅ ሆኖ እንዲተላለፍ የጎላ ድርሻ አላቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በፅሁፍ ላይ ስርዓተ ነጥቦች አስተካክሎ ካለመጠቀም የተነሳ ዐ.ነገሮች ያሻማሉ ፤ መልክቶች ይዛባሉ ፤ ሃሳቦች ይድበሰበሳሉ፡፡ ስለዚህ ሃሳቦችን ግልፅ በሆነ መንገድ በፅሁፍ ለማስተላለፍም ሆነ የተፃፈውን መልዕክት በትክክል አንብቦ ለመረዳት ስርዓተ ነጥቦችንና አገልግሎታቸውን በሚገባ ማወቅ ተገቢ ይሆናል፡፡

### የስርዓተ ነጥብ ዓይነቶች

በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ በርካታ ስርዓተ ነጥቦች ይገኛሉ ፡፡ ምንነታቸውንና አገልግሎታቸውን ቀጥለን እንመልከት፡፡

- **አንድ ነጥብ ወይም ይዘት (.)** ፦ ይህ ስርዓተ ነጥብ አንድን ቃል ወይም ሐረግ አሳጥሮ

ለመፃፍ የሚያገለግል ሲሆን ይህም የማሳጠር ስልት ምህፃረ ቃል ወይም አፅሮተ ቃል በመባል ይታወቃል፡፡

**ምሳሌ** ፦ አ.አ.ዩ. ፣ ኦ.ል.ማ. ፣ ከ.ነ.ማ.

ሌላው ብርና ሳንቲምን ለመለየት **ምሳሌ** ፦ 10.50 ፣ 100.50

ክፍልፋይ ቁጥሮችን ለመለየት ምሳሌ፡ 7.5፣ 10.5

- **ሁለት ነጥብ ( ፡ )** ፦ ቃልን ከቃል ለመለየት የሚያገለግል ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ብዙም አገልግሎት ላይ ሲውል አይታይም፡፡

ሌላው የሁለት ነጥብ አገልግሎት ሰዓትን ከደቂቃ ለመለየት ያገለግላል ለምሳሌ ፦ ነገ 3፡30 ላይ ቢሮ እንድትመጣ፡፡

- **ስስት ነጥብ ( . . . )** ፦ ይህ ስርዓተ ነጥብ በርከት ያሉ አገልግሎቶች ያሉት ሲሆን ፣ በዐ.ነገር መጀመሪያ ላይ፣ መካከልና መጨረሻ ላይ ሊገባ ይችላል፡፡

**ምሳሌ፦** ሲኒማ ተያይዘን የምንገባው፣ ዋና የምንዋኘው፣ ፈረስ ግልቢያ የምንለማመደው ሔ ትዝታው ከፊቴ እየመጣ ድቅን ይልብኛል፡፡

ሌላው ፀያፍ የሆነ አባባልን ላለመፃፍ ስንፈልግ ነጠብጣብ በማድረግ እንተወዋለን

ለምሳሌ፦ አላርፍ ያለች ጣት . . .

እንዲሁም በልቦለድ ውስጥ አንድ ደራሲ ገፀባህርይው ኃይለኛ የመረበሽ፣ የመርበትበት፣ የመደሰት ፣ ወዘተ ስሜት ውስጥ እንደገባ ለመግለፅ ሶስት ነጥብን ይጠቀማል፡፡

ምሳሌ፦ “እኔ . . . አ . . . አ . . . አላምንም እንድ . . . እንድንጋባ ወሰንክ!”

- **አራት ነጥብ ( ፡፡ ) ፦** አንድ ሀሳብ ወይም ዐ.ነገር መቋጨቱን ለማመልከት ያገለግላል፡፡

**ምሳሌ ፦** ምንግዜም የአሸናፊነት ስሜት አይቀንስም፡፡

ስብሰባው የተጀመረው ዘግይቶ ነው፡፡

- **ነጠላ ሠረዝ( ፣ ) ፦** የሚዘረዘሩ ነገሮችን ለያይተን ለማስቀመጥ ያገለግላል፡፡

**ምሳሌ** ፦ አያና ፣ ጫላ ፣ ገለታ ፣ ቢቂላ የቶለሳ ወንድሞች ናቸው፡፡

ነጠላ ሠረዝ የሚለየው ቃልን ከቃል ብቻ ሳይሆን የማያስሩ ዐ.ነገሮችን ለመለየት ያስችላል።

**ለምሳሌ** ፡- እንጨት ሰብሬ ፣ ውሃ ቀድቼ ፣ እህል ፈችቼ እዲሁም ልብስ አጥቤ መኖር መሮኛል።

እንዲሁም የመፃፍን ምዕራፍና ቁጥር ለመለየት ምሳሌ ፡- ሉቃ 4 ፣ 5

❖ **ድርብ ሠረዝ ( ፤ )** ፡- ራሳቸውን የቻሉ ተመሳሳይ ድርጊቶችን የያዙ ዐ.ነገሮች ተከታትለው ሲመጡ ድርብ ሰረዝን እንጠቀማለን ምሳሌ ፡- እንጨት ሰበርኩ ፤ ውሃ ቀዳሁ ፤ ልብስ አጠብኩ ፤ ስለዚህ ማረፍ አለብኝ ።

ከዚህ በተጨማሪ ሁለት የተለያዩ ሀሳቦችን በአያያዥ ቃላት ከመጠቀማችን በፊት ድርብ ሠረዝ መጠቀም እንችላለን ።

ምሳሌ ፡- ሒሳብ አይገባኝም ፤ ነገር ግን ከማጥናት አልቆጠብም።

ደመናው ከብዷል ፤ ስለዚህ ዝናብ ሊዘንብ ይችላል።

❖ **ጥያቄ ምልክት ( ? )** ፡- አንድን ሀሳብ በጥያቄ መልክ ለማስተላለፍ ያገለግላል።

ምሳሌ ፡- ወንድምህ መጣ።

ወንድምህ መጣ?

ቋንቋ ምንድን ነው?

❖ **ትዕምርተ ጥቅስ (“ “ )** ፡- ይህ ስርዓተ ነጥብ በልቦለድና ፊልም ፅሁፎች ውስጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

1. የተለያዩ ገፀ ባህርያትን ንግግር ለይቶ ለማስቀመጥ

ምሳሌ፡ “ ከቤታችሁ ያለው ካሴት ይህ ብቻ ነው?”

“ያልከውን አደረኩልህ እኮ “

“ ሌላ ቀይሪልኝ”

“እሺ የማንን ፈለክ”

2. የሰዎችን ሀሳብ እንዳለ ከወሰድን በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ማስቀመጥ ይኖርብናል።

ምሳሌ፡ “ ሰውን ሰው ያሰኘው ስራ ነው”

3. ከዚህ በተጨማሪ ትኩረት የሚሹ ቃላትንና የተውሶ ቃላትን በጥቅስ ውስጥ ልናስቀምጥ እንችላለን

ምሳሌ ፡ በንፅህና ጉድለት ምክንያት በ"ታይፎይድ"እና "ታይፈስ"በሽታ ብዙ ሰዎች ይጠቃሉ፡፡

❖ **ነጠላ ጥቅስ(‹ ›)፡-** በጥቅስ ውስጥ የሚገኝን ሌላ ጥቅስ ለማመልከት ይረዳል፡፡አንድ ሰው የተናገረውን በሶስተኛ ወገን ሲነገር በነጠላ ትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ ይቀመጣል፡፡

**ምሳሌ፡-** የትምህርት ቤታችን ርዕሰ መምህር ፣ “ወጣቶች ! ትምህርት የችግሮች ሁሉ መፍቻ ቁልፍ ነው፤ ሌኒን ‹መማር መማር አሁንም መማር› እንዳለው ሳትዘናጉ በርትታችሁ መማር ይኖርባችኋል፡፡"በማለት ለተማሪዎች አስገነዘቡ፡፡

❖ **ትዕምርተ አንክሮ(!)፡-** የመደሰት ፣ የመገረም ፣ የመቆጣት ፣ የማዘን ፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን ኃይለኛ ስሜቶች ለመግለፅ የሚያገለግል ነው፡፡

**ምሳሌ፡-** አንተ እርጉም ከፊቴ ጥፋ!

ድህነት ቀንደኛ ጠላታችን ነው!

ኦ! ከበደ ከየት መጣ!

❖ **ትዕምርተ ስላቅ (¡)፡-** አንድን ሀሳብ በፌዝ ፣ በተሳልቆ ወይም በምፀት መልክ ለማስተላለፍ ስንፈልግ የምንጠቀመው የስርዓተ ነጥብ ዓይነት ነው፡፡ **ምሳሌ** ፡- ፀጉሯ ዞማ ነውሸ

ቁመቱ መሰላል ያህላልሸ

❖ **ቅንፍ** ( )፡- በፅሁፍ ውስጥ ወይም የሚለውን ቃል ተክቶ ይገባል፡፡ ምሳሌ፡- ዛሬ(ነገ)እመጣለሁ፡፡

ዋናውን ቃል የሚያብራራ አማራጭ ቃልን ወይም ሀረጋትን በዐ.ነገር ውስጥ ስናስገባ

ቅንፍን እንጠቀማለን ፡፡

**ምሳሌ፡**- አሽከርካሪዎች (ሾፌሮች)በሙሉ ለትራፊክ ህግ ሊታዘዙ ይገባል፡፡

- **ንዑስ ሠረዝ(- )**፡- ሁለት ቃላትን ያጣምራል፡፡ ምሳሌ፡- ፀረ-ተባይ ፣ ቤተ-መንግስት
- **ዐብይ ሠረዝ (-)፡-** እስከ የሚለውን ቃል ተክቶ ይገባል፡፡

ምሳሌ፡- ከሰኞ- ሐሙስ ድረስ ስራ የለኝም፡፡

ከሀረር - አዲስ አበባ በባቡር መጣሁ፡፡

- **ቋሚ ሠረዝ(/)፡-** ረጃጅም ቃላትንና ሀረጋትን ለማሳጠር ፣ አማራጭ ፍቺ ለመስጠት ፣ ተራ ቁጥሮችን ወይም ቅደም ተከተል የያዙ ነጥቦችን በሆሄያት ለመዘርዘር ያገለግላል፡፡

ምሳሌ ፡- ታክሲ/አውቶብስ መጠቀም ትችላለህ፡፡

ዐ/ነገር ፣ ዶ/ር

- **ሁለት ነጥብና አግድም ንዑስ ሠረዝ(፡-)፡-** አንድ ዐ.ነገር ከመገታቱ በፊት ዝርዝር ነጥቦችን የሚያስከትል ከሆነ ወይም ለምሳሌ፣ ለማስረጃና ለማሳያ ከሚዘረዘሩ ነጥቦች ቀድሞ ግልጋሎት ላይ ይውላል፡፡

**ለምሳሌ፡-** የኪነ ጥበባት ዓይነቶች በርካታ ሲሆኑ፤ አንዳዶቹን ለመጥቀስ ያህል ፡- ስነ ፅሁፍ ፣ ስነ ስዕል ፣ ቴአትር ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## ድርሰት

ድርሰት የሚባለው ምናባዊ የፈጠራ ስራ ብቻ እንዳልሆነ ልብ ልንል ይገባል፡፡ በመሆኑም ድርሰት አንድን ነገር ምናባዊ ወይም ነባራዊ በሆነ መንገድ የምንገልፅበት የፅሁፍ ዘርፍ ነው፡፡

- ✓ ምናባዊ ስንል አንድን መልዕክት ኪናዊ በሆነ መልኩ በአንባቢው አእምሮ ውስጥ ምስል ለመከሰት ሲባል የተመረጡ ቃላትን በመጠቀም የምናስተላልፍበት ስልት ሲሆን፣
- ✓ ነባራዊ ስንል ደግሞ በገሀዱ ዓለም የሚታየውን ነገር እንዳለ ማቅረብ ማለት ነው፡፡

## የጥሩ ድርሰት ባህርያት

- ጥሩ ድርሰት አጭር ፣ ግልፅ እና ማራኪ ርዕስ ይይዛል፡፡
- የተመረጡ ፣ ውብና ሳቢ ቃላትን ይጠቀማል ፡፡
- አንድነት፣ ግጥምጥምነትና ብርታት ባላቸው አንቀፆች ይገነባል፡፡
- አገነባቡ ተያያዥነት ባላቸው አንቀፆች ተከፋፍሎ ይቀርባል ፡፡
- ተኣማኒነት ባለው ሀሳብ ላ ብቻ ያተኩራል፡፡
- ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ በተገቢው ቦታ ይጠቀማል፡፡
- ያለምንም ችግር እንዲነበብ ሆኖ ይፃፋል፡፡

ጥሩ የድርሰት ርዕስ የሚባለው፡-

- ✓ እጥር ምጥን ያለ
- ✓ ሳቢ
- ✓ ከድርሰቱ ዋና ሀሳብ ጋር ተያያዥነት ያለው
- ✓ ለማስታወስ የማያስቸግር ነው፡፡

ሌላው በድርሰት ውስጥ መነሳት ያለበት ጉዳይ አስተዋፅኦ ነው፡፡ አስተዋፅኦ አንድ ድርሰት ከመፃፉ በፊት በውስጡ ምን ምን ጉዳዮች መነሳት እንዳለባችው የሚዘጋጅ ንድፍ ወይም መዋቅር ነው፡፡ አስተዋፅኦ መንደፍ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

- በፅሁፉ ውስጥ መነሳት ያለባቸው ጉዳዮች እንዳይዘነጉ ያደርጋል፡፡
- የተነሱ ሀሳቦች በድጋሚ እንዳይነሱ በማድረግ የሀሳብ ድግግሞሽን ያስወግዳል ፡፡
- የምንፅፈው ድርሰት የድርጊት ቅደም ተከተል ወይም የተስተካከለ የሀሳብ ፍሰት እንዲኖረው ያግዛል፡፡

## የድርሰት ዓይነቶች

የድርሰት ዓይነቶች አራት ናቸው፡፡ አነሱም፡-

- ❖ ተራኪ ድርሰት

- ❖ ገላጭ ድርሰት
- ❖ ስዕላዊ ድርሰትና
- ❖ አመዛዛኝ ድርሰት ናቸው።

**ተራኪ ድርሰት** ፦ አንድን ነገር በትረካ መልክ እንዲህ ሆነ፤ ከዚያም እንዲህ ተፈጠረ እያለ የሚተርክ የድርሰት ዓይነት ነው።

- መሰረት የሚያደርገውም ባለፉ ጉዳዮች ላይ ነው።
- ታሪኩን የሚገግረንም እራሱ የድርጊቱ ተካፋይ ሊሆን ይችላል ። አለበለዚያም ድርጊቱን የተመለከተ የደረሰበት በልምድ ያገኘው ፤ ከሌላ ሰምቶ የሚያቀርበው ሊሆን ይችላል።

**ምዕራፍ አራት**

## 4. ልቦለድ

ልቦለድ ከደራሲው ምናባዊ ፈጠራ የሚመነጭ የሰውን ህይወት ልዩ ልዩ መልኮች በተመሳስሎ ለመቅረፅ የሚችል በቁሙ ግን እውነት ያልሆነ የኪነ ጥበብ ስራ መሆኑን እንገነዘባለን። ልቦለድ የገሃዱን ዓለም የሰው ልጆች የህይወት ውጣ ውረድ ስቃይና ደስታ ማግኘትና ማጣት ፣ እረሀብና ጥጋብ ፣ ህመምና ጤና ፣ተንኮልና ቅንነት ፣ ወዘተ መነሻ በማድረግ በደራሺ ለጸደራሺ የሚቀርብ ጥበባዊ የፈጠራ ስራ ነው።

ልቦለድ የገሀዱ ዓለም ህይወት ነፀብራቅ ነው። ለዚህም ነው በልቦለድ ውስጥ የምናገኛቸው ገፀባህርያት ሲያዝኑ የምናዝነው፤ ሲደሰቱ የምንደሰተው።

### 4.1. የልቦለድ ዓይነቶች

ልቦለድ በሁለት ይከፈላል። እነሱም አጭርና ረጅም ልቦለድ ናቸው።

#### 4.1.1. ረጅም ልቦለድ

አንደ ዘሪሁን አስፋው ገለፃ “ረጅም ልቦለድ ከደራሲው ምናባዊ ፈጠራ የሚመነጭ የሰውን ህይወት ልዩ ልዩ መልኮች በተመሳስሎ ለመቅረፅ የሚችል በቁሙ ግን እውነት ያልሆነ የኪነጥበብ ስራ መሆኑን እንገነዘባለን። ልቦለድ በቁሙ እውነት አይደለም ሲባል የተተረከው የገፀባህርያት ህይወት በእውኑ አለም በእርግጥ የተፈጸመ አይደለምለማለት ነው። “

### 4.1.2. አጭር ልቦለድ

እንደ ዘሪሁን አስፋው ገለፃ “አጭር ልቦለድ በዝርው የተፃፈ፣ በጠበቀ አንድነት የተዋቀረ አብዛኛውን ጊዜ በጥቂት ቃላት የሚቀርብ የፈጠራ ባህርያትን የተላበሰ ስራ ነው።”

አጭር ልቦለድ የማህበረሰቡን ገጠመኝ መሰረት በማድረግ አንድ ነጠላ ውጤት ያለው ጥቂት ገፀ ባህርያት ያሉት በግዜና በቦታ የተመጠነ ግጭት ያለው በአንድ ቁጭታ ተነቦ የሚያልቅ ኪነታዊ የፈጠራ ፅሁፍ ነው። ባጠቃላይ አጭር ልቦለድ መቼቱ ጠባብ የሆነ ፣ ከልደት እስከ ሞት የማተርክ ፣በአንድ ጭብጥ ላይ የሚያጠነጥን ውበት ያለው የፈጠራ ስራ ነው።

### 4.2. የአጭር ልቦለድና የረጅም ልቦለድ ልዩነት እና ተመሳሳይነት

| አጭር ልቦለድ | ረጅም ልቦለድ |
|---|---|
| ገፀ ባህርያቱ ጥቂት ናቸው | ብዙ ገፀ ባህርያት ያሉበት ነው |
| የያዘውን ታሪክ እስኪጨርስ ይጣደፋል | ሳይጣደፍ በዝግታ ታሪኩን ያቀርባል |
| የታሪኩ ድርጊት የሚፈፀምበት ጊዜና አካባቢ ውሱንና አጭር ነው። | በተለያ ቦታዎች ድርጊቱ ስለሚፈፀም መቼቱ ሰፊ ነው |
| የድርጊቱ ግጭት ፈጣን መፍትሄ ይሻል። | መፍትሄውን ለማቅረብ አይጣደፍም በርካታ ግጭቶች ይኖሩታል። |
| ከአንድ ነጠላ ታሪክ በተጨማሪ ንዑሳን ታሪኮች አይኖሩትም። | አንድ አብይ ታሪክ ይኖረውና እሱን የሚያጎለብቱ ታሪኮች ይኖሩታል። |
| ታሪክን በስፋት የመተረክ አቅም የለውም | ታሪኮችን በስፋት ያቀርባል ከልደት እስከ ሞት የመተረክ አቅም አለው። |

ሁለቱ የልቦለድ ዓይነቶች የሚያመሳስላቸው ሁለቱም የፈጠራ ፅሁፍ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ሁለቱም የልቦለድ አላባውያን አላቸው።

### 4.3. የልቦለድ አላባውያን

ልቦለድን ስናነሳ በውስጡ የምናነሳቸው በርካታ የልቦለድ አላባውያን አሉ። እነሱም ፡- ታሪክ፣ ገፀ ባህርያት ፣ ግጭት ፣ መቼት ፣ ጭብጥ ፣ አንፃርና ትልም ናቸው።

- ❖ **ታሪክ ፡-** የአንድ ልቦለድ ቀዳሚው ነገር ታሪክ ነው። የልቦለዱ መሰረት ነው። የልቦለዱን ታሪክ እንዲህ ሆነ፣ ከዚያም እንደዚህ ሆነ ፣ በመጨረሻም እንዲህ ሆነ ብለን የምንተርከው የልቦለድ ታሪክ ይባላል።

❖ **ገፀ ባህርያት ፡-** በገሀዱ ኣለም ውስጥ ያሉ ሰዎችን ወክለው እንደ ሰው የሚደሰቱ ፣ የሚያዝኑ ፣የሚራሩ ፣ የሚጨነቁ፣ የሚያፈቅሩ፣ የሚራቡ፣ የሚጠሙ ፣ የሚታመሙ ፣ የሚሞቱ፣ ወዘተ. ደራሲው በምናቡ የሚፈጥራቸው ፍጡራን ገፀ ባህርያት ይባላሉ፡፡

❖ **መቼት፡-** በልቦለድ ውስጥ ያሉ ገፀ ባህርያት ልክ እንደ እውኑ አለም ሰዎች ቤት፣ አካባቢ ፣ ሀገር አላቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪም ገፀ ባህርያቱ አንድን ድርጊት የሚያከናውኑበት ሰዓት ፣ ቀን ፣ ወር፣ ዓመት ይኖራቸዋል፡፡ ስለዚህ መቼት ማለት በልቦለድ ውስጥ ያሉ ገፀ ባህርየት ድርጊቱን የፈፀሙበት ጊዜ እና ቦታ ነው፡፡

❖ **ግጭት፡-** በነባራዊው ዓለም ውስጥ የሚኖሩ የሰው ልጆች በፍቅርና በመተሳሰብ እንደሚኖሩ ሁሉ በተቃራኒው አንዱ አንዱን ጠልፎ ለመጣል ፣ አንዱ ሌላኛውን ለመበቀል ፣ ለማጥቃት ፣ ወዘተ. ሴራ ሲሸርቡ ፣ ተንኮል ፣ ሲጠነስሱ፣ ሲዶልቱና ሲያሴሩ እንደ ሚኖሩ ሁሉ በልቦለድ ውስጥ ያሉ ገፀ ባህርያትም ይህንኑ ይፈፅማሉ፡፡ ይህ የገፀ ባህርይት ፍጭት ግጭት ይባላል፡፡

❖ **ጭብጥ፡-** አንድን የፈጠራ ስራ አንብበን ከጨረስን ቦሃላ ካነበብነው ፅሁፍ የምናገኘው መልዕክት ጭብጥ ይባላል፡፡ ማንኛውም ደራሲ ለመፃፍ ከመነሳቱ በፊት መጀመሪያ የሚያስጨንቀው ጉዳይ ለአንባቢው የሚያስተላልፈው ፍሬ ነገር ወይም ጭብጥ ነው፡፡ በአጠቃላይ ደራሲው ከህይወት ልምዱ በመነሣት ፣ በሚኖርበት ህብረተሰብ ውስጥ ያየውን ፣ የታዘበውን ነገር በማስመልከት በተዋጣና ለዛን በተላበሰ ሁኔታ የሚያስተላልፈው መልዕክት ጭብጥ ይባላል፡፡

❖ **ትልም፡-** ታሪኩ ከየት ተነስቶ ወዴት እንደሚሄድ ፣ የታሪኩ መቋጫ ምን እንደሆነ ፣ በጊዜ ቅደም ተከተል እየተሰናሰነ የሚነግረን የሁነቶች ትረካ ነው፡፡ ይህም የሁነቶች ትረካ በምክንያትና ውጤት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ምን ለምን ተደረገ? ብለን ስንተጠይቅ የምናገኘው ምላሽ ነው፡፡

❖ **አንፃር ፡-** ማንኛውም ልቦለድ _ደራሲውና በአንባቢው መካከል ሆኖ ሁነቶችን የሚገልፅና የሚተረጉም ፣ አልፎ አልፎ በግልፅ አብዛኛውን ጊዜ ግን በውስጠ ታወቂ የሚኖር_የታሪኩን ህይወት እየተከታተለ የሚያቀርብ ተራኪ አለው፡፡ ተራኪው ታሪኩ የሚመለከተው ተሳታፊ ወይም ታሪኩ የማይመለከተው ታዛቢ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም አንፃር ታሪኩን የሚተርከው ማን ነው? ታሪኩ የተተረከው ከምን አኳያ ነው? የሚለውን ጉዳይ የሚመለከት ነው፡፡

ከዚህ አኳያ የተለያየዩ የአንፃር ዓይነቶች አሉ ፡፡ እንሱም፡- ሁሉን አወቅ አንፃር ፣ ውሱን ሁሉን አወቅ አንፃር ና አንደኛ መደብ አንፃር ናቸው፡፡

- **ሁሉን አወቅ አንፃር ፡-** ይህ የአንፃር ዓይነትገፀ ባህርያቱ ምን እንደሰሩ፣ ምን ችግር እንደገጠማቸው ፣ ምን እንዳሰቡ ሳይቀር ዝክዝክ አድርጎ የሚያቀርብ ነው፡፡የሚያቀርበውም በሶስተኛ መደብ ሲሆን ገፀ ባህርያቱ እንዲህ ሆኑ ፣ እንዲህ አሰቡ ፣ይህን በሉ፣ ይህን ጠጡ ወዘተ. እያለ ያቀርብልናል፡፡
- **ውሱን ሁሉን አወቅ አንፃር፡-** ይህ የአንፃር አይነት ልክ እንደ ሁሉን አወቅ አንፃር ሁሉ በሶስተኛ መደብ የሚተረክ ነው፡፡ይሁን እንጂ የገፀ ባህርያትን ስሜት፣ ፍላጎት፣ ምኞት፣ አያውቅም፡፡ ይህም ማለት ገፀ ባህርያቱን በተመለከተ ያለው ግንዛቤ ውሱን ነው፡፡ ሆኖም ገፀ ባህርያቱ ከሚናገሩት፣ ከሚያደርጉት ከእንቅስቃሴያቸው በመነሳት እንዲህ አደረጉ ፣ ይህን ፈጠሩ በዚህ ወጡ፣ በዚህ ወረዱ፣ ወዘተ. በማለት ያቀርባል፡፡
- **አንደኛ መደብ አንፃር፡-** ከዳር ቆሞ ገፀ ባህርያቱ የሚያደርጓቸውን ድርጊቶች እየተከታተለ የሚያቀርብ ነው፡፡ ተራኪው የሰዎችን ድርጊት ብቻ ሳይሆን የራሱንም ገጠመኝ ጭምር እንዲህ ሆንኩ፣ እንዲህ አደረግሁ እያለ ያቀርብልናል፡፡

## ክርክር

ክርክር ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች የመከራከሪያ ርዕሳቸውን መርጠው፣ ዳኛ፣ እንዲሁም ክርክሩን የሚከታተሉ ታዳሚዎች በተገኙበት ማራኪ በሆነ አቀራረብና አሳማኝ በሆነ መልኩ የሚያደርጉት የንግግር ስልት ነው፡፡

### የክርክር አዘገጃጀት መመሪያ

- ለክርክር በሚቀርበው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ መረጃዎችን መሰብሰብ
- ለመከራከሪያ የተዘጋጀውን ሀሳብ በቅደም ተከተል ማዋቀር
- ክርክሩን ከማቅረብ በፊት ልምምድ ማድረግ
- አሸንፋለሁ የሚል በራስ የመተማመን ስሜት ማዳበር
- የተሟላ ስብዕና ይዞ መቅረብ

### የክርክር አቀራረብ መመሪያ

- ✓ የመከራከሪያ ርዕስን ለአድማጮች ማስተዋወቅ፣
- ✓ ያለ ምንም መረበሽና መርበትበት በሙሉ ልብ ለማቅረብ መሞከር ፣
- ✓ ክርክሩን ሊያጎሉ የሚችሉ ምሳሌዎችን፣ አባባሎችን መጠቀም፣
- ✓ አላስፈላጊ የሆኑ የአካል እንቅስቃሴዎችን ማስወገድ፣
- ✓ ከተቃዋሚ የሚሰጡትን ሀሳብ በጥሞና ማዳመጥ፣ ማስታወሻ መያዝ፣
- ✓ ክርክሩን በተሰጠው የጊዜ ገደብ ለማጠናቀቅ መሞከር፣
- ✓ ክርክሩ ሲያልቅ ለአድማጮች ምስጋና ማቅረብ።

## አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት/ሐረጋት

አንቀፆች አንድነትና ግጥምጥምነት ይኖራቸው ዘንድ አያያዥ ቃላትና ሐረጋት ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። አያያዥ ቃላትን ሐረጋት ዐ.ነገርን ከዐ.ነገር ፣ አንቀፅን ከአንቀፅ በማያያዝ የምናነሳው ሐሳብ ፍሰቱን በጠበቀ መልኩ እንዲተላለፍ ያደርጋሉ።

በአማርኛ አያያዥ ቃላት ከሚባሉት ውስት ጥቂቶቹን እንሆ፡- ምክንያቱም፣ አለበለዚያ፣ ዳሩ ግን፣ እንደገና፣ ቢሆንም፣ ይሁን እንጂ፣ በአንፃሩ፣ ነገር ግን፣ በተለይ፣ በመጨረሻም፣ በተመሳሳይ፣ የሆነ ሆኖ፣ ወዲያው፣ ይህ በእንዲህ እያለ፣ እንጂ፣ ግን፣ ስለዚህ፣ ያም ሆነ ይህ፣ ይልቅ፣ ይህ ደግሞዬ

እያንዳንዳቸው አያያዥ ቃላትና ሐረጋት የራሳቸው ቦታና አገልግሎት አላቸው። በመሆኑም አንዱ በገባበት ቦታ ሌላው ቢገባ ዓ.ነገሩ ሊዛባ፣ሀሳቡ ሊፋለስ ይችላል።

ምሳሌ፡- ስለዚህ

ነገር ግን

ሀ. በደንብ አጥንቻለሁ፤--------------------- ጥሩ ውጤት አመጣለሁ።

ለ. ቡና ሲፈላ ደስ ይለኛል፤ ------------------ ስጠጣ አይስማማኝም።

በምሳሌ ‗ሀ‘ስር በቀረበው ዓ.ነገር ውስጥ መግባት ያለበት አያያዥ ቃል ‗ስለዚህ‘ ነው። በሱ ቦታ ላይ ‗ነገር ግን‘የሚለውን ብናስገባ ሀሳቡ የተዛባ ይሆናል።

**መልመጃ**

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አያያዥ ቃላትና ሐረጋት ቀጥሎ በቀረበው ባዶ ቦታ ውስት በማስገባት አንቀፁ የተስተካከለ የሀሳብ ፍሰት እንዲኖረው አድርጉ፡፡

ሀ. ነገር ግን　　መ. እና　　ሰ. ይሆን ዘንድ

ለ. ስለዚህ　　ሠ. እርግጥ ነው

ሐ. ቢሆንም　　ረ. ያለምክንያት

ሰው ከተሰማራ እንደየ ስሜቱ ፣

በዋለበት ሥፍራ አይቀርም ማፍራቱ የተባለው ----------- አይደለም ፡፡የሰው ልጅ በስራው ደስተኛ ----------- ውጤታማ ----------- እንደየ ፍላጎቱ መሰማራት አለበት ፡፡ ----------- የዕለት ጉርሱን ላለማጣት ሲል እየመረረው ---------------- ሊሰራ ይችላል፡፡ -------------- ስራውን የሚሰራው ያለፋላጎት በመሆኑ ውጤቱ አመርቂ አይሆንም፡፡ --------------- የፍላጎት መኖር ብቻ ሳሆን ችሎታም ትልቅ ድርሻ አለው፡፡

**የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች**

አንዳንድ የአምርኛ ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች አሏቸው፡፡

**እማሬያዊ ፍች**፡- ቶሎ ወደ አእምሮአችን የሚመጣልን ትርጉም ዌም የቃሉ ቀትተኛ ፍች ነው፡፡

ምሳሌ ፡- ወነወበር ስንል ቶሎ ወደ ጭንቅላታችን የሚመጣው መቀመጫ ነው፡፡ አልጋ ስንል የቃሉ ቀጥተኛ ፍች መንታ ነው፡፡ ከእነዚህ ውች ያለውን ትርጉም ለማወቅ የቋንቋ ተናጋሪውን ብስለት የሚጠይቅ ነው፡፡

**ፍካሬያዊ ፍች፡-** ከቃሉ ቀጥተኛ ትርጉም ባሻገር የምናገኘው ፍች ነው፡፡አንድ ሰው ዌም የቋንቋው ተናጋሪ ቃሉ ሲጠራ ቢያንስ እማሬያዊ ትርጉሙን ያውቃል፡፡ወንበር ምንድነው ሲባል መቀመጫ የሚል መልስ ይሰጣል፡፡ነገር ግን ስልጣን የሚል ትርጉም እንዳለው ላያውቅ ይችላል፡፡ ምክንያቱም ፍካሬያዊ ትርጉም ነውና፡፡ ከዚህ አንፃር የሚከተሉትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ያላቸውን ቃላት እንመልከት፡፡

| **ቃል** | **እማሬያዊ ፍች** | **ፍካሬያዊ ፍች** |
|---|---|---|
| ንብ | ክንፎች ያላት፣ ማር አምራች<br>በራሪ ፍቱር | ትጉህ፣ ታታሪ፣ ሰራተኛ |

| | | |
|---|---|---|
| አልጋ | መኝታ | ዙፋን፣ ዘውድ |
| ኩራዝ | ለመብራት የሚያገለግል | አጭር |
| ድንክ | ትንሽ አልጋ | አጨር |
| ምላጭ | የፀጉር መላጫ | ብልጥ |
| በግ | የቤት እንሰሳ | ሞኝ ፣ ገራገር |
| ምሰሶ | የቤት ዋና ደጋፊ | አባወራ |
| ቀዳዳ | የተሸነቆረ | ነገር የማይቋትር |
| እንጀራ | ምግብ | ሀብት፣ አዱኛ |
| ቤት | መኖሪያ | ትዳር |
| ወንፊት | የዱቄት መንፊያ | ሚስጢር የማይቋጥር |

## የቃል ክፍሎች

በዘመናዊ ሰዋስው የቃል ክፍሎች በአምስት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም፡- ስም ፣ ግስ ፣ ቅፅል፣ ተውሳከ ግስና መስተዋድድ ናቸው፡፡

የቃል ክፍሎች አምስት ናቸው ስንል የትኛውም ቃል ወስደን የቃል ክፋሉን ብንመረምረው ከላይ ከተዘረዘሩት ከአምስቱ ውጭ ኤሆንም ማለታችን ነው፡፡ ቀጥለን እያንዳንዱን እንመልከት

**ስም፡-** የአንድ ነገር መጠሪያ ነው፡፡ የሰዎች ፣ የእንሰሳት ፣ የዕፅዋት ፣ የረቂቅና የግዑዝ ነገሮች መጠሪያ ስም ይባላል፡፡ ስሞችን በአምስት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

- ✓ የተፀውኦ ስም
- ✓ የቁሳቁስ ስም
- ✓ የወል ስም
- ✓ የጥቅል ስም
- ✓ የረቂቅ ስም

**የተፀውኦ ስም፡-** የማንኛውም ነገር የግል መጠሪያ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ሞክሼ (ተመሳሳይ ስም) አይኖርም ማለት አይደለም፡፡

ምሳሌ፡- ካሳ፣ ቶላ፣ ኢትዮጵያ፣ አባይ፣ ወዘተ.የተፀውኦ ስሞች ናቸው፡፡

**የወል ስም፡-** በአፈጣጠራቸው ወይም በዓይነታቸው ተመሳሳይ የሆኑ ሁሉ በጋራ የሚጠሩበት ስያሜ ነው፡፡

ምሳሌ ፡- ወጣት        በግ        ወንዝ

ሰው        በቅሎ        ሀይቅ

**የጥቅል ስም፡-** ይህ የስም ዓይነት የተለያዩ ስሞችን በውስጡ ጠቅልሎ ይይዛል፡፡ በዚህ ስም ውስጥ የተፀውኦ እንዲሁም የወል ስሞች ተካተው ይገኛሉ፡፡

ምሳሌ፡- ሰራዊት        መዓድን        ህዝብ

**የቁሳቁስ ስም፡-** የሰው ልጆች ለመገልገያነት የሚጠቀሙባቸውን መሳሪያዎች የሚመለከቱ ስሞች ናቸው፡፡ እነዚህ ስሞች ከወል ስሞች ጋር ይመሳሰላሉ፡፡

ምሳሌ፡- አልጋ        ወንበር        ጠርሙስ        ኩባያ        ወዘተ.

**የረቂቅ ስም ፡-** ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው በህሊና የሚታወቁ ፣ ነገር ግን በእጅ የማይዳሰሱ ፣ በዓይን የማይታዩ መጠሪያ ስያሜ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ፍቅር ፣ ጨለማ ፣ ዕውቀት፣ ሞት፣ ብርሃን፣ እውነት፣ ውሸት፣ ወዘተ.

አንድን ቃል ስም ነው ለማለት የራሱ የሆነ መስፈርት አለው፡፡ እነዚህም መስፈርቶች አገባብ ና ቅርፅ ናቸው፡፡

- ✓ ከቅርፅ አንፃር ስናየው ስሞች አብዢ ምዕላድን ይወስዳል፡፡

ምሳሌ፡- ልጅ        ልጆች

- ✓ አገባብን ስንመለከት ደግሞ፡- በዐ.ነገር ውስጥ ተሳቢ ወይም ባለቤት በመሆን ይገባል፡፡

  ምሳሌ፡- ህፃኑ መፅሃፉን ቀደደ፡፡   ህፃኑ ባለቤት  ፣ መፃሃፉን ተሳቢ ነው፡፡

- ✓ ሌላው ጠቃሚ ወይም መጣኝ መስተዓምርን ይወስዳል፡፡

  ምሳሌ፡- ያ ልጅ        እነዚያ ልጆች

  ሁለት ልጆች        ብዙ ልጆች

**ግስ፡-** አብዛኛውን ጊዜ በዐ.ነገር መጨረሻ ላይ በመገኘት ሀሳባችንን ሊቋጭ የሚችል

ቃል ግስ ይባላል። ግሶች ድርጊት አመልካች ቃላት ተብለው ይጠራሉ። በአማርኛ አንድ ቃል ግስ ለመሆኑ ማረጋገጫ ሁለት መስፈርቶች አሉት እነሱም አገባብና ቅርፅ ናቸው።

- ✓ ከአገባብ አንፃር ስናይ ፦ በዐ.ነገር መጨረሻ ይገኛል።
- ✓ ከቅርፅ አንፃር ሲታይ ደግሞ የባለቤት አፀፋዎችን ይይዛል።

ለምሳሌ፡- በላ ፣ ሰበረ ፣ ሞተ ፣ሔሔ

**ቅፅል፡-** ከስም በፊት በመግባት ስምን የሚገልፅ የቃል ክፍል ነው። ይሁን እንጂ ስምን ቀድሞ የገባ ሁሉ ቅፅል ሊሆን አይችልም። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

ለምሳሌ፡- **ትልቅ** በግ

**ይህ** በግ

**ቶላ የገዛው** በግ

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ እንደምናየው ትልቅ ፣ ይህና ቶላ የገዛው የሚሉት በግ የሚለውን ስም ቀድመው ገብተዋል። ከነዚህ ውስጥ ግን ቅፅል ሆኖ የምናገኘው ትልቅ የሚለውን ብቻ ነው። ይህን ሁኔታ ለማረጋገጥ በምሳሌዎቹ ላይ በጣም የሚለውን ቃል ብንጨምር የሚከተለውን እናገኛለን።

ሀ. በጣም ይህ በግ x

ለ. በጣም ትልቅ በግ

ሐ. በጣም ቶላ የገዛው በግ x

“ሀ” ና “ሐ” ላይ የሚገኙት ተቀባይነት የለውም “ለ” ላይ ያለው ተቀባይነት አለው። ስለዚህ አንድን ቃል ቅፅል መሆን አለመሆኑን በሚከተለው መፈተሻ ልናረጋግጥ እንችላለን።

በጣም ------------- ስም

**ተውሳከ ግስ፡-** ከግስ በፊት በመግባት ግስን የሚገልፅ የቃል ክፍል ነው። ግስን የሚገልፀው ደግሞ ከጊዜ ፣ ከቦታ ፣ ከሁኔታ ወዘተ. አንፃር ነው። ነገር ግን ግስን የሚገልፁ ሁሉ ተውሳከ ግስ ናቸው ማለት አይደለም ምክንያቱም የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት

ምሳሌ፡- ቶላ <u>ወደ ነቀምት</u> ሄደ።

ጫላ <u>በሩጫ </u>መጣ።   ወደነቀምት እና በሩጫ የሚሉት ግስን ይገልፃሉ ነገር ግን ቃል ሳይሆኑ ሐረግ ናቸው። ሀረግ ደግሞ በቃል ክፍልነት ሊመደብ አይችልም። ሐረግ ከቃልበላይ ነውና። በቋንቋው ውስጥ የሚገኙት ተውሳከ ግሶች በጣም ጥቂት ኛቸው። የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ገና ፣ ከፉኛ ፣ ምንኛ ፣ ቶሎ ፣ ግምኛ ፣ ጅልኛ

**መስተዋድድ፡-** መስተዋድድ ማለት ቃልን ከቃል ፣ ሀረግን ከሀረግ ፣ እንዲሁም ዐ.ነገር ከዐ.ነገር የሚያዋድድ፣ የሚያስማማ ማለት ነው። መስተዋድድ የተጓደለበት ሀረግ ወይም ዐ.ነገር ምሉዕነት አይኖረውም።

መስተዋድድ የሚባሉት ከ ፣ ወደ፣ ስለ፣ እንደ፣ ጋር፣ ሴ

መስተዋድድ የቃል ክፍል ከሌሎች የቃል ክፍል የሚለየው ለተለያዩ ሰዋስዋዊ ባህርያት ቅርፃቸውን አይቀይሩም በመሆኑም እንደሌሎች የቃል ክፍሎች ሌላ ቃል አይመሰርቱም ፤ ከሌላ ቃልም አይመሰረቱም።

**ሐረግ**

- ሐረግ ማለት ቃላት በስርኣት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት መዋቅር ነው።
- ከቃል ሰፋ ያለ መዋቅር ነው።

በአማርኛ ቋንቋ የሐረግ ዓይነቶች አሉ። እነሱም ፡-

- ✓ ስማዊ ሐረግ
- ✓ ግሳዊ ሐረግ
- ✓ ቅፅላዊ ሐረግ
- ✓ ተውሳከ ግሳዊ ሐረግና
- ✓ መስተዋድዳዊ ሐረግ ናቸው።

ስማዊ ሐረግ፡- የሀረጉ መሪ ቃል ስም የሆነ የሐረግ ዓይነት ነው።

የሐረጉ መሪ ቃል በቀኝ በኩል ይገኛል።

ምሳሌ፡- የማር <u>ጠጅ</u>

የዶሮ <u>ወጥ</u>

የሸክላ ሳህን

ጠጅ ፣ ወጥ፣ ሳህን ፣ የሚሉት የሐረጉ መሪ ቃላት ስሞች በመሆናቸው ሐረጉን ስማዊ ሐረግ እንለዋለን።

**ግሳዊ ሐረግ፡-** የሐረጉ መሪ ቃል ግስ የሆነ የሐረግ ዓይነት ነው። የሐረጉ መሪ ቃል በቀኝ በኩል ይገኛል።

ምሳሌ፡- ለበዓል በግ ገዛሁ።

ፈተናውን በጥሩ ሁኔታ አለፈ።

ገዛሁ፣ አለፈ የሚሉት ቃላት ግስ ናቸው። በመሆኑም የሀረጉ መሪ ቃል ግስ በመሆኑ ሀረጉ ግሳዊ ሐረግ ነው።

**ቅፅላዊ ሐረግ፡-** የሐረጉ መሪ ቃል ቅፅል የሆነ የሐረግ ዓይነት ነው። በቅፅላዊ ሐረግ የሀረጉ መሪ ቃል የሚገኘው በቀኝ በኩል ነው።

ምሳሌ፡- ሁሉም ሰው እንደ ንብ ታታሪ መሆን አለበት።

ቶላ እንደ ወንድሙ ጎበዝ ተማሪ ነው።

**ተውሳከ ግሳዊ ሐረግ፡-** የሐረጉ መሪ ቃል ተውሳከ ግስ የሆነ የሐረግ ዓይነት ነው። የሐረጉ መሪ ቃል የሚገኘው በቀኝ በኩል ነው። ምሳሌ፡- ልጁ ክፉኛ ታመመ።

የእረፍት ሰዓት ገና ነው።

**መስተዋድዳዊ ሐረግ፡-** ይህ ሐረግ ከሌሎቹ የሚለይበት ዋነኛ ባህሪው መሪው ቀኝ ወይም ግራ መሪ ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል ከመሪው ብቻ ሐረግ ሊመሰረት አይችልም።

ምሳሌ፡- ከወንድሙ ጋር

በፍጥነት

**መልመጃ**

**የተሰመረባቸውን ሐረጎች የሐረግ ዓይነታቸውን ግለፁ**

1. አበላሉ ክፉኛ ያስጠላል።
2. አሳው ከባህር ወጣ።
3. ከወንድሙ ጋር ወደ ት/ቤት ሄደ።

4. <u>ትልቅ የወርቅ ቀለበት</u> ጠፋባት።

5. ትልቅ አንበሳ <u>ሁለት ላሞች ገደለ</u>።

6. <u>እንደ እህቱ የዋህ</u> ነው።

7. <u>ካሳ እንደ አባቱ ክፉኛ</u> ታመመ።

8. ጫላ <u>ለመሄድ ገና</u> አልተዘጋጀም።

**ዘይቤ**

- ዘይቤ ለአገላለፅ ትኩስነትና ጥንካሬ ለመስጠት ሲባል ከመደበኛው የቃላት ፍች ወይም የቃላት አደራደር ስርዓት ይሁነኝ ብሎ ማፈንገጥ ነው።

- ዘይቤ አንድን ነገር የመግለፅ የቃላትና የሀረጋትን ትርጉምና አገባብ ከተለመደውና በውል ከታወቀው ወጣ ወይም ለየት በማድረግ ለሀሳብ ላቅ ያለ ደረጃ ወይም ከፍታ በመስጠት ነው።

- ዘይቤ የሚፈጠረው አንድን ባህሪ፣ ስሜት ፣ድርጊት ፣ ሁኔታ ሰው ወይም እንሰሳትን ከሌላ ነገር ጋር በማወዳደር ከማመሳሰል አንዱን ባህርይ ለሌላ በመስጠት ወይም በመለወጥ የአንድን ባህሪ በመቅዳትና አንድን ነገር በሌላ ለመወከል ነው።

- ዘይቤ አንድን የሰው ባህርይ ስሜትና መልክ አጉልቶና አድምቆ ለተመልካቹም ሆነ ለሰሚው ምናባዊ ፍሰሃ በመስጠጥ የሚያቀርብ የአነጋገር ስልት መሆኑን ብዙ አዋቂዎች ይናገራሉ።

ዘይቤ ከተራው አነጋገር ይበልጥ ግብመችነት የሚሆነው በምን የተነሳ ነው? ለዚህ 3 አብይ ምክንያቶች አሉ።

1. ዘይቤ ምስል ከሳች ከተራው አነጋገር ከፍ ያለና የናረ በመሆኑ አስደሳች ስሜትን ሊፈጥር በመቻሉ።

2. ረቂቁን ነገር ተጨባጭ በማድረግ የስሜት ቅርብነት እንዲኖረውበማድረግ

3. በጥቂት ቃላት ብዙ ሀሳብ ታጨወቆ እዲቀርብ በማድረግ የዕምቅነት ባህርይ በማጎናፀፉ ነው።

በአማርኛ ቋንቋ በርካታ የዘይቤ አይነቶች አሉ። ይሁን እንጂ ለዚህ የክፍል ደረጃ ብቻ የሚመጥኑትንና የተዘወተሩትን የዘይቤ ዓይነቶች በዝርዝር እንመለከታለን።

- ✓ ተነፃፃሪ ዘይቤ
- ✓ ተለዋጭ ዘይቤ
- ✓ ሰውኛ ዘይቤ
- ✓ ግነት ዘይቤ
- ✓ እንቶኔ ዘይቤ
- ✓ ምፀት ዘይቤ
- ✓ አያው ዘይቤ

- ➢ **ተነፃፃሪ ዘይቤ፡-** በተለያየ ጎራ ያሉ ሁለት ነገሮችን በመውሰድ በመካከላቸው ያለውን ተመሳስሎ ለማሳየት እያነፃፀረ የሚያቀርብ የዘይቤ ዓይነት ነው።ዋና ዓላማውም በአድማጭ ወይም በኣናባቢው አእምሮ ምስል መፍጠር ነው። በሚነፃፀሩት ሁለት የተለያዩ ነገሮች መካከል አንድ የሚያመሳስላቸው የጋራ ባህሪ ሊኖር ይገባል። ይህም የጋራ ባህሪ ሰበበ ንፅፅር ይባላል።

ምሳሌ፡- የቶላ ፊት የሐምሌን ጨለማ ይመስላል።

ጫልቱ እንደ ፀሐይ ታበራለች።

ልጁ ቁርጥ አባቱን ይመስላል።

አነፃፃሪ ዘይቤ ሁለት ነገሮችን በሚያነፃፅርበት ጊዜ እንደ ፣ ያህል፣ ይመስላል የሚሉ ማነፃፀሪያዎችን ይጠቀማል።

- ➢ **ተለዋጭ ዘይቤ፡-** ይህ ዘይቤ ቃሉ እንደሚያመለክተው የአንዱን ባህርይ ለሌላው በመስጠት ፣ በመለወጥ የሚፈጠር የዘይቤ ዓይነት ነው። ከአነፃፃሪ ዘይቤ ጋር የመመሳሰል ባህርይ ቢኖረውም እንደ አነፃፃሪ ዘይቤ እንደ ፣ ይመስላል፣ ያህላል፣ የመሳሰሉትን ማነፃፀሪያዎች አይጠቀምም።

ምሳሌ፡- አበበ አንበሳ ነው።

ልጁ አሳማ ነው።

ተለዋጭ ዘይቤ ቀደም ብለን እንዳየናቸው የዘይቤ ዓይነቶች ሁሉ በአረፍተ ነገር ብቻ ሳይሆን

በግጥም ውስጥም ይቀርባል።

- **ሰውኛ ዘይቤ፡-** የሰውን ልዩ ልዩ ባህሪያት ድርጊትና ችሎታ ሰው ላልሆኑ ነገሮች ፣ ለእንስሳት፣ ለተክሎችና ለግዑዛን በመስጠት የሚፈጠረው ዘይቤ ሰውኛ ዘይቤ ይባላል።

ምሳሌ፡- እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አለች አህያ

ጨለማው ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ።

አህያና ጨለማ ሰው አይደሉም ፤ ይሁንና  አህያ እንደሰው ስትናገር ጨለማ እንደሰው ሲያለቅስ ተመልክተናል። እንደ ሰው ሆነው ሰው የሚፈፅመውን ተግባር ሲያከናውኑ እናያለን ለዚህም ሰውኛ ዘይቤ እንለዋለን።

- **ግነት ዘይቤ፡-** ትንሽ እውነታን በመያዝ አተልቆ ወይም አግዝፎ የሚያቀርብ የዘይቤ ዓይነት ነው። ግነት ውሸት አይደለም።

ምሳሌ፡- ቤቱ ፈረስ ያስጋልባል።

ዝሆን የሚያክል ቁንጫ ገደልኩ።

- **እንቶኔ ዘይቤ፡-** ይህ ዜይቤ ሰው ያልሆነ ነገሮች የሰውን ባህርያት አላብሶ ማቅረቡ ከሰውኛ ዘይቤ ጋር ያመሳስለዋል። በአቀራረቡ ግን ይለያያሉ። እንቶኔ በሁለተኛ መደብ ሲያቀርብ ሰውኛ ግን በሶስተኛ መደብ ያቀርባል። ሌላው እንቶኔ ዘይቤ አጠገብ የሌለን ነገር ቅርብ እንዳለ በመቁጠር መልስ እንዲሰጥ፤ሀሳብ እንዲሰነዝር በመጠየቅ ፣ በማወያየት ፣ በማጫወት የሚቀርብ ዘይቤ ነው።

ምሳሌ፡- ተናገር አንተ ሀውልት

እባክሽ አንቺ ምድር ፍረጂኝ

- **ምፀት ዘይቤ፡-** አንድን መልዕክት በፌዝ፣ በሹት፣ ወይም በተሳልቆ መልክ ለማስተላለፍ ስንፈልግ የምንየቀምበት የአገላለፅ ስልት ነው። በዚህ ዘይቤ የሚገለፀውን ነገር መረዳት ያለብን ፊት ለፊት ያለውን ሳይሆን በተቃራኒው ነው።

ምሳሌ፡ በጣም አጭር ሰው ዛፉ መጣሽ

በጣም ቀርፋፋን ሰው ከጀት ይፈጥናልሽ

- **እያዎ ዘይቤ፡-** ይህ ዘይቤ አይ ና አዎ የሚሉ ሁለት ተቃራኒ ሀሳቦችን የያዘ የቋንቋ አጠቃቀም ስልት ነው፡፡እያዎ ዘይቤ ላይ ላዩን ሲመለከቱት እውነትነት የሌለው ተራ ሀሳብ የያዘ የሚመስል ዌም ሁለት የተጣረሰ ሀሳብ የያዘ ሲሆን ጠለቅ ብለው ሲመረምሩት እውነት የሆነ መልዕክት የሚያስተላልፍ የዘየቤ ዓይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡ ካልደፈረሰ አይጠራም፡፡

ያለ ጦርነት ሰላም የለም!

እያዎ ዘይቤን ለመረዳት ጠለቅ ያለ ምርምርን ይጠይቃል፡፡

## መልመጃ ዘይቤ

**የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች እና ግጥሞች በየትኛው የዘይቤ ዓይነት እንደቀረቡ መልስ ስጡ፡፡**

1. በቅሎዬ ስገሪ እንግባ ሀገራችን፣

   የመጣንበቱ አልቋል ጉዳያችን፡፡
2. እንደ ሀምሌ እንደ ነሀሴ እንደወዲያኛው፣

   ልቤን ክፍት ክፍት አለብኝ ምነው፡፡
3. ‹‹እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል››አለች አህያ
4. የሰራው ቤት ፈረስ ያስጋልባል!
5. ምነው አዲስ አበባ ጭንቅሽ በዛ
6. ጫልቱ ነብር ነች፡፡
7. አባይ ሮጦ ሮጦ ግብፅ ሲደርስ ይደክምና ያርፋል፡፡
8. ግቢው ባህር ነው፡፡
9. እንደ ሰማይ ኮከብ ታበራለች፡፡
10. ይህ ቀን ፊቱን አዞረብኝ፡፡

11. ረሀቤ ጥማቴ ርዛቴ ሶስቱ፣

ይደበድቡኛል ባንድ እየዶለቱ።

12. በበሩ ጀርባ ተደብቄ አንገቱን ብይዘው ሞቶ ተነሳ።

13. ፈጥነህ ከሄድክ አትደርስም ረጋ ብለህ ከሄድክ ግን ትደርሳለህ።